የሰ/መ/ቁ. 60542

የካቲት 27 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ሓጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ተክለድንግል ገ/ሚካኤል

ተጠሪ፡- የፌ/ሥ/ም/ፀ/ሙስና ኮሚሽን አቃቤ ሕግ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የሙስና ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካችና በሌሎች ስምንት ሰዎች ላይ በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡የአሁኑ አመልካች የተከሰሱት በአንድ መዝገብ በተከፈተ ክስ ሲሆን የክሱ ይዘትም አመልካቹ በ1996 ዓ/ም በወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1ሀ)፣33 እና 407(1(ሀ)(ሐ))፣(2) እና (3) ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመተላለፍ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራሱ ለማግኘትና በመንግስትና በሕዝብ ጥቅም ላይ ከፍተኛ የሆነ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ በስር ፍርድ ቤት ቀደም ሲል አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተመድቦ ሲሰራ በነበረበት ወቅት በስራው አጋጣሚ በእጁ የገባውን የአዲስ አበባ ከተማ ማስተር ፕላን ከስራ ሲታገድ በሲዲ በመገልበጥና በኮምፒዩተር በመታገዝ በከተማው ውስጥ ያሉትን ክፍት ቦታዎችን በመለየትና ቀደም ሲል በነበረው ስርዓት ለማኅበራት ይፈቀድ የነበረውን የቤቶች ፕላን ቶፖሎጂ በወቅቱ በከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር የሚሰራባቸውን የቤቶች አይነት በፕላን በማዘጋጀት ሕጋዊ ያልሆኑ ማህበራትን ከሕግ ውጪ በማደራጀትና ቦታን በመስጠት የሙስና ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ በአንደኛ ተራ ቁጥር ተከሳሽ ከነበረው ከአቶ በሃይሉ ለማ ድንቁ ጋር በጥቅም በመመሳጠር በሐሰትና በተቀነባበረ ዘዴ "ሻላ" የሚባል ሃሰተኛ የመኖሪያ ቤት የሕብረት ስራ ማህበር እንዲቋቋም አድርጎ በሀሰተኛ መንገድ የተዘጋጀው የማህበሩን ፋይል ከስር ሁለተኛ ተከሳሽ(ወ/ሮ ደሃብ ገ/ሕይወት) ጋር የጥቅም ግንኙነት በመፍጠር በ1998 ዓ/ም የካ ክፍለ ከተማ ማህበር ማደራጃ ፅ/ቤት ውስጥ እንዲገባ በማስደረግና የማህበሩ አባላትም የተሳሳተ ግንዛቤ እንዲኖራቸው እና ማህበሩን ሕጋዊ አስመስሎ በማቅረብና በሁለተኛ ተከሳሽ በኩል ሃሰተኛውን ማህበር ሕጋዊ አስመስሎ እንዲነገር አድርጎ 248 የማህበሩ አባላት በሕገ ወጥ መንገድ መሬት እንዲያገኙ በማድረግና ቦጋለ የተባለውን ሐሰተኛ እና ሕገ ወጥ ማህበር ፋይልም ከ1ኛ ተከሳሽ በመቀበል ለሁለተኛ ተከሳሽ ሰጥቶ ወደ ክፍለ ከተማው ማህበራት ማደረጃ ፅ/ቤት እንዲገባ አድርጎ በሁለቱም ሐሰተኛ ማህበራት ሕገ ወጥ ጥቅም በማግኘት፣በማስገኘትና በመንግስትና በሕዝብ ጥቅም ላይ ከፍተኛ የሆነ ጉዳት በማድረስ የሙስና ወንጀል ፈፅሟል የሚል ነው፡፡ጉዳዩ አግባብነት ባለው ስነ ስነ ሥርኣት ተመርቶ አመልካች ክሱን በመካድ በመከራከራቸውም አቃቤ

ሕግ አሉኝ ያላቸውን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቧል፡፡የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎች ተመርምረውም አመልካች "ሻላ" የሚባል የመኖሪያ ቤት ሕብረት ማህበር ሊቀመንበር ለመሆናቸው አቃቤ ሕግ ባቀረበው የሰነድ ማስረጃ ማስረዳቱ መረጋገጡን ፍርድ ቤቱ ገልፆ ይህንኑ እንዲከላከሉ ተደርጎ አመልካች በበኩላቸው አሉኝ ያሏቸውን ማስረጃዎችን ለመከላከያ ማስረጃነት አቅርበዋል፡፡ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም አመልካች በመከላከያ ማስረጃዎቹ የአቃቤ ህግን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን ሊያስተባብሉ ያልቻሉ መሆኑን በመግለፅ በአቃቤ ሕግ የክስ ማመልከቻ ተጠቅሶ የቀረበባቸውን ድንጋጌ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 113(2) መሰረት ዝቅ አድርጎ አመልካችን በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ አንቀጽ 32(1(ሀ))፣33 እና 407(1(ሀ)) ስር ጥፋተኛ አድርጎአል፡፡ከዚኅም በኋላ የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ከተቀበለ በሁዋላ አመልካችን በአምስት አመት ፅኑ እስራትና በብር 5,000.00(አምስት ሺኅ ብር) የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ወስኖባቸዋል፡፡በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች መስከረም 18 ቀን 2003 ዓ/ም በጻፉት አምስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ይዘቱም ባጭሩ፡-አመልካች የመንግስት ሰራተኛ ሳይሆኑ በሙስና መከሰሳቸው ያላግባብ መሆኑን፣በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 141 ነጻ በተባሉበት ጉዳይም ተመልሶ ጥፋተኛ መባላቸው ስነ ሥርኣቱን ያልጠበቀ መሆኑን፣የስር ፍርድ ቤት በአመልካች እንዲቀርብና ፊርማው እንዲመረመር የተጠየቀውን የሰነድ ማስረጃ በፎረንሲክ ሳያስመረምር አልፎ ውሳኔ መስጠቱም የማስረጃ አቀራረቡና አመዛዘኑ ሥርዓት ሕጉን ያልጠበቀ መሆኑን የሚያሳይ መሆኑን ዘርዝርው በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሳኔ ተሽሮ አመልካች በነጻ እንዲሰናበቱ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች የቤት ስራ ማህበር ሊቀመንበር ናቸው ተብሎ ጥፋተኛ መደረጋቸው ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎል፡፡በዚህም መሰረት ተጠሪ የካቲት 15 ቀን 2003 ዓ/ም በተጻፈ ማመልከቻ መልሱን ሰጥቷል፡፡ አመልካች በበኩላቸው መጋቢት 09 ቀን 2003 ዓ/ም በተጻፈ ማመልከቻ የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለአቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ላይ ከጠቀሷቸው የቅሬታ ነጥቦች መካከል አንዱ ተጠሪ ክሱን በማስረጃ አለማስደገፉንና አመልካች እንዲመረመርላቸው የጠየቁት ሰነድ በፎረንሲክ ሳይመረመር እንዲሁም ለተሰሙት የመከላከያ ምስክሮች ቃል ክብደት ሳይሰጥ መታለፋን የሚመለከት ነው፡፡ይሁን እንጂ በዚህ ረገድ የቀረበው ቅሬታ በሰበር ችሎት እንዲታይ በጭብጥነት ያልተያዘ ከመሆኑም በላይ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች የግራ ቀኙን ማስረጃ በማጣራትና በመመዘን የአመልካችን የመከላከያ ማስረጃዎችን የአቃቤን ህግን ማስረጃዎችን የማስተባበል ብቃት የላቸውም በሚል ያለፉት ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት የተሰጠው ሥልጣን በበታች ፍርድ ቤቶች በተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ

መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ማረም በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበውን ቅሬታ ይህ ችሎት የሚመረምረው ሁኖ ስላላገኘው አልፈነዋል፡፡

ሌላው አመልካች ያቀረቡት ቅሬታ አመልካች የመንግስት ሰራተኛ ሳይሆኑ በሙስና ወንጀል መከሰሳቸው አዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 7 ድንጋጌን በግልፅ የሚጻረር ነው በሚል ነው፡፡ይሁን እንጂ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡት ቅሬታ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 33 ድንጋጌን መንፈስና ይዘት ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ ምክንያቱም አመልካች በስር ፍርድ ቤት የተከሰሱት የመንግስት ሰራተኞቾ ጋር የጥቅም ትስስር በመፍጠር በመንግስትና በሕዝብ ጥቅም ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሰዋል በሚል ከመሆኑም በላይ በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 33 መሰረት አንድ ሰው የመንግስት ሰራተኛ ባይሆንም በሙሉ ፈቃዱና እውቀቱ የሙስና ወንጀል ሙሉ ተካፋይ መሆኑ ከተረጋገጠ በሙስና የሚከሰስበት አግባብ መኖሩ የተደነገገ ነውና፡፡

በዚህ ችሎት እንዲታይ የተያዘውና አመልካች በመከራከሪያነት ያቀረቡት ሌላው ነጥብ አመልካች የቤት ማህበሩ ሊቀመንበር ናቸው በማለት ጥፋተኛ መባላቸው ተገቢ መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች የተከሰሱት ሕጋዊ ያልሆኑ ማህበራትን የሊቀመንበርነት ስልጣን አለኝ በማለት አደራጅተው ለማህበሩ አባለት ያላግባብ ቦታ እንዲሰጥ አድርገዋል፣በዚህም በመንግስትና በሕዝብ ጥቅም ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሰዋል በሚል ሲሆን የማህበራቱ ሕጋዊ አለመሆንና ማህበራቱ ሲደራጁ እንዲሁም ቦታውን ሲወስዱ አመልካች የነበራቸው ሚና ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ነጥብ ነው፡፡በመሆኑም የቤቱ ማህበራት ሕጋዊ ያለመሆናቸውና የተደራጁትም አመልካች በሊቀመንበርነት በነበራቸው ሚና ጭምር መሆኑ ከተረጋገጠ አመልካች በወንጀል የማይጠየቁበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ሌላው አመልካች በዚህ ድርጊታቸው ነጻ ተብለው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 141 የተሰጠ ብይን የሌለ መሆኑን የስር ፍርድ ቤትን መዝገብ አስቀርበን የተመለከትን በመሆኑ በዚህ ረገድ የተነሳው ቅሬታም እውነትነት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡በአጠቃላይ በአመልካች ላይ የተሰጠው የጥፋተኛነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 60587 ሚያዚያ 04 እና 14 ቀን 2002 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 56628 ሰኔ 29 ቀን 2002 ዓ/ም የፀናው የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195((2(ለ-2)) መሰረት ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡
2. በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረት ቅጣቱን ተከታትሎ ያስፈፅም ዘንድ ውሳኔው መፅናቱ ለማ/ቤቱ ይገለፅለት ብለናል፡፡ይፃፍ፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ አምስት የዳኞች ፊርማ አለበት